# <u>የቀይ ሽብር ጠበቆች</u>

*መስፍን መሃመድ - ከ አዶላ ወዩ*

ከቅርብ ግዜ ወዲህ ስለ ነጻው የፕሬስ ህጎችና ዑደቱ ብቅ ብቅ ያሉ አንዳንድ አስተያየቶች ከኮሎኔል መንግሥቱ መጽሃፍ ጋር ተያይዘው የመጡ አዳዲስ ሃሳቦችን ተመልክቼ እንደወትሮዬ ዝም ብዬ ማለፍ ስላልቻልኩበት ዛሬም እጄን ላነሳና የችሎታዬን ልዳስስ ግድ ሆኖብኛል::

አንዳንዴ ስለ ኢትዮጵያዊነት ሳስብ ግርም የሚያደርገኝን ነገር መልሼ እንደገና አስበውና መልሶ ደሞ ግርምምም ያደርገኛል:: ኢትዮጵያ አልታደለችም ተብላ በአለም ማህበረሰብ ዘንድ በጽኑ የታወቀችበት በአንድ ዘመን ተፈጠረ …………መነሻውም መድረሻውም የደም ዘመን!

የቀድሞ መሪዎቹን ከየቤታቸውና ከያሉበት እያወጣ እንዳሻው ከረሸነ በኋላ በህዝቡ ሙሉ ፈቃድ እንደሆነ አድርጎ ለፈፈ:: በዚህ ጊዜ ደርግ የሚስቅበትም የሚስቀልትም ተመልካች አተረፈ፡፡ ወዲያውም ብዙዉን የተማረ ክፍል ለሞትና ለእስር ዳረገ:: ይህኔ አለም ሳቀች ………..

ወጣቱን ከየቤቱ እያነቀ እያወጣ ራቁቱን ሜዳላይ ረፈረፈው:: አሁን ደሞ ምድር አለቀሰች። ወላጆች አነቡ:: ለልጆቻቸው ሞት ሀዘንን እንኳ ተነፈጉ። ዋይታ ምድሪቷን ከበባት። ድንጋጤና ሀዘን ነገሠ:: ኢትዮጵያ የደም ምድር ሆነች:: የዋይታ ምድር ሆነች። ሃገሪቱን ሊገነባ የሚችለው ምሁር እየታደነ ተቀጠፈ። የኢትዮጵያ ተስፋ የሚሆነው ወጣት እየተለቀመ ተጨፈጨፈ። ወላጅ ስለልጆቹ ምድሪቱን ኮነነ:: ወልደን ካላሳደግንብሽ አንቺ አገር አትባረኪ አሏት።

**ግፍ በሀገር ናኘ**
**ኩበት ጠልቆ ድንጋይ ዋኘ !** ……………………….ተብሎም ስንኝ ተቋጠረ !

በውነት ይህቺ ሃገር እርግማን አለባት የሚሉት ነገር ውነት ይሆን? እልናም ያስፈራኛል:: ድሮ ድሮ ልጅ ሳለሁ መንግሥቱ ነዋይኮ በአደባባይ ሲሰቀል ኢትዮጵያን "አንቺ ምድር ወንድ አይብቀልብሽ“ ብሎ ረግሚታል ሲሉ ሰምቼ - "እንዴ! እሱ ምናገባውና ይራገማል? ጃንሆይ ናቸው እንጂ?“ - ብለህል ስትል እናቴ ባስታወሰችው ቁጥር ትስቅብኝ ነበር ::

በኋላ በኋላ ነገሩ ሲገባኝ ግን መንግሥቱ ነዋይ ይህቺን ቃል የተናገረው ፈጽሞ ለእውነት የተነሳ የለውጥ ሀዋርያ እንደነበረና የነገስታቱ አድርባዮች ምን ያህል እንዳሳመሙት ያሳያል:: ምክንያቱም ሀሰተኛ ቢሆን ኖሮ "አምላኬ ሆይ ነፍሴን ተቀበላት" ይል ይሆናል እንጂ በአድርባይ ቅጥረኞች የተነሳ በሃገሩ አያዝንም ነበር …………. ይለኛል ኀሊናዬ::

ባለፈው የ"ደራሲ" ተስፋዬ ገብረአብን አንድ የዘለፋ ጽሁፍ አንብቤ፣ እዚያው ገጹ ስር አጠር ያለች መልስ ጽፌ ነበር፡

ደራሲ ተስፋዬ ገብረአብ ይህንንው አስመልክተው ሰው ሲያረጅ አይተው እንደሚያውቁና ፓርቲ ሲያረጅ ግን የመጀመሪያ ግዜያቸው እንደሆነ …….. በማለት በዘመናዊ የጽሁፍ ቋንቋ ሊያቆሽሹ መጣራቸውን አንብቤያለሁ::

እውቀት በሽሙጥ የሚመዘን ቢሆን እመርቃቸው ነበር:: ዳሩ ግን ደራሲ ወይንም ጸሃፊ ከህሊናው በሚያፈልቀው ጥበብ አንባቢን ይማርካል እንጂ ............... !

አያይዘውም እኔ በኢህአፓ ጊዜ ጨቅላ ነበርኩኝ ይሉና:: ካደግሁ በኋላ ግን ስለ ኢህአፓ ለማወቅ ስፈልግ አቦይ ስብሃት ነገረኝ ሲሉ፤ አሁን ስለሚራገሙበት ችሎታቸው ያረጋግጡልናል:: ደግነቱ ያኔ ጨቅላ ስለነበሩ ምንም ነገር ስለማያውቁና መመስከር ስለማይችሉ፤ ካደጉ በኋላ አቦይ ስብሃት የነገሯቸውን ነው ተቀብለው የጻፉት እንጂ፤ እንደ አንዳንዶች ሥህተት ጸሃፊዎች የማውቀው እና ያየሁትን ነው የጻፍኩት ብለው ቢናገሩ ኖሮ ቁጭቴ ገባ ያለ በሆነ ነበር::

እኔ ግን እልዎታለሁ - ጥሩ ተናጋሪ እንጂ ጥሩ አድማጭ አይመስሉኝም:: ምክንያቱም አቦይ ስብሃትን እና ወላጅ እናትዎን ያወዳደሩበት ሚዛን ሽፋፋ ነው::

ዋናው ቁም ነገር ኢህአፓን መውቀስዎ አለመውቀስዎ ለኔ ምንም ማለት አይደለም። ቢወዱም ቢደግፉም የግል ምርጫዎ ብቻ ነው:: ፓርቲ ያለተቃዋሚ ሊኖር እንደማይችል ሁሉ እርግጠኛ ነኝ ማንም አያመውም::

ይሁን እንጂ በምን አመካኝቶ እንዲሉ ለአረመኔው መሪ ለመንግሥቱ ኃይለማሪያም ያለዎትን አቋም በማየቴና በአደባባይ ሊሟገቱለት በመነሳትዎ ጽሁፍዎ ዝምታዬን አሸንፎታል::

ለህዝብና ለሃገር አንድነት፣ ለፍትህና ለነጻነት ሲሉ በንዳድ ጸሃይ በአደባባይ በጥይት የተደበደቡትን፣ ደማቸው እንደጎርፍ የፈሰሰውን፣ በልጆቻቸው ሬሳ ላይ እንዲጨፍሩ የተገደዱትን ወላጅ እናቶችን፣ በልጆቻቸው ሞት የጥይት ዋጋ እንዲከፍሉ የተገደዱና ፍትህ አጥተው እድሜያቸውን ሙሉ በሃዘን ለኖሩና ላለፉ ወላጆች እንዲህ ያለ ዋጋ ቢስ ምላሽ ማሳየትዎ ምንኛ አሳዛኝ ልቦና እንዳለዎ ፍርዱን ለአንባቢ እተዋለሁ:: መንግሥቱ ኃይለማሪያምን በቀጥታ የኢህአፓ ጠላት ብቻ አድርገው የሚመለከቱ ፍጹም ድሀ የሆነ መገንዘብ ስላላቸው ሰዎች አዝናለሁ::

የሆነው ሆኖ እያንዳንዱ በመንግሥቱ ኃይለማሪያም ሥርዓት ትዕዛዝ የተረሸነው፣ በእሳት የተቃጠለው፣ በድብደባ የተሰቃየው፣ በዘይት የተጠበሰው፣ አስፋልት ላይ የተገደለው፣ አካሉን ያጣው፣ ወዘተ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ነጻነት እኩልነትና አንድነት ሲል ነው! የዚህ ዓላማ ጠላት ደግሞ መንግሥቱ ኃይለማሪያም ነው! እኔ ያንን 17 ዓመታት እንዴት ብዬ እንደገና እንደምገልጸውና በምንስ ቃላት ተናግሬ እንደምጨርሰው አላውቅም፤ አልችለውምም:: ከሰላሳ ዓመታት ሳይዘል እንዲህ ያለ የታሪክ ጠላት ተነስቶ ለሀገሩና ለህዝቡ ሲል ራሱን የሰዋ ትውልድ የሚዘለፍበት ጊዜ ላይ መድረሳችን እጅግ አድርጎ ያሳዝነኛል::

በደንብ አስታውሳለሁ:: ብዙዎች ሃገር ውስጥ የነበራችሁና የምታስታውሱም አላችሁ:: ደርግ ከስልጣን እንደሸሸ በመላው ሃገሪቱ እንቅስቃሴዎች ተነስተዋል:: ባጭሩ እኔ በነበርኩበት አካባቢ ወላጆች የልጆቻቸውን ፎቶግራፎች እየያዙ የልጆቻችን ደም ይጮሃል! ገዳዮቻቸው ለፍርድ ይቅረቡ! የሚል ሰልፍ አድርገዋል:: ሁኔታውንም በደንብ አውቃለሁ:: ኢህአዴግም ወዲያው እያሳደደ ጥሩ ምላሽ የሚሰጥ መስሎ ነበር:: ዳሩ ይሄው ዛሬ ጭራሽ መጽሃፋቸውን አሳትሞ ለገበያ አቅርቦላቸዋል! ያም ሆነ ይህ ይህ ጥያቄ መቼም ይሁን መቼ አይቀርም! ኢህአዴጎችም መቼም መቶ አመት አትኖሩ እናንተም አንድ ቀን ትሄዳላችሁ ::

ሌላው በፕሬስ የምታሳብቡ ስለ ፕሬስ ነጻነት ከአራት አስርተ ዓመታት ጀምሮ ያስተማረ ማን እንደሆነ የያኔዋን ዴሞክራሲያ አፈላልገው ያንብቧት። ዳሩ እርስዎ ያኔ ህጻን ነበሩና አያውቁትም:: አሁንም አቦይን ለመጠየቅ እንዳይሄዱ ጊዜዎን ለመቆጠብ እኔ ልንገርዎ::

እንኳንስ ኢህአፓን የሚያህል ለሃገሩና ለወገኑ ራሱን የሰጠ ፓርቲ ቀርቶ፣ ዛሬ ማንም ሰው የፕሬስን ምንነት ጠንቅቆ ያውቃል። የመናገርን እና የመጻፍን ነጻነት ይወዳል። ፕሬስ የህዝብ አንደበት ነው! እርስዎ በማያውቁት ዘመን ራሱን ለፍትህ የሰጠው ትውልድ ዴሞክራሲን በማወቁ ነው!!! በውነት እርስዎ ይህንን ሊያስተምሩን ፈልገው ከሆነ መጀመሪያ እራስዎን ይጠይቁ ! ዛሬ የእድገት ጫፍ ላይ የደረሱ ሃገሮች የነበሯቸው ጨካኝና አምባገነን መሪዎቻቸው የተጠሩበት ስም እንኳ ዳግመኛ የሃገሪቱ ዜጋ እንዳይጠራበት ህግ አርቅቀው ያጸደቁ ሃገሮች እንዳሉ ያውቁ ይሆን? እኔ እርስዎም ሆኑ ሌሎች እንደ እርስዎ ለኮሎኔሉ የቆሙ ሁሉ የሚያውቁ አይመስለኝም ምናልባት ብታውቁ የምትሉትን በሰማሁ አሰኝቶኛል:: ምክንያቱም የኢትዮጵያውን አረመኔ አምባገነን ስሙን ልታድሱለት ሩጫ መጀመራችሁ ግራ አጋብቶኛልና !

ዛሬ ዛሬ አንዳንድ ሰዎች የተሰውለት ፓርቲ አብሯቸው ተቀብሯል ብለው የሚጽፉትን አልፎ አልፎ አነብባለሁ:: ደርግ በነበረው ጠመንጃና ጥይት ሁሉ የሚችለውን ከፈጀ በኋላ ኢህአፓ አብቅቶለታል እያለ ይለፍፍ እንደነበረ ደሞ እኔም ትዝ ይለኛል:: ስለዚህ የተለወጠ አዲስ መልክት የሌለው ያው ከሰላሳ ዓመት በፊት የምትሉትን ነው አሁንም የምትደግሙት ምንም አይጠቅምም:: እንደውም የወያኔ የፖለቲካ መንፈስ እንደእሾህ የተሰካባቸው እንኳን አንዳንዴ ሲባንኑ እናያለን:: ምክንያቱም ያው የመንግስቱና የስራ አስፈጻሚዎቹ ዕጣ አይቀሬ ስለሆነ ይመስለኛል::

ደርግ በመላው ዓለም ኢትዮጵያዊ ዲፕሎማቶችን ሲልክ ከጎኑ የነበሩትን ሚሊቴሪዎች ሲቪል እያደረገ በሚፈልግባቸው ቦታዎች አስቀምጧቸዋል::
በወቅቱ ገናና በነበሩ የሶሻሊስት ሃገሮች እንደ ሶቭየት ኅብረት፣ ቼኮዝሎቫኪያ፣ ምስራቅ ጀርመን እና ሌሎችም የሚሊቴሪ አታሼዎች እየተሾሙ ብዙ የደርግን ሥራ ሰርተዋል:: ለነሱ ብቻም ከሌላው ህዝብ የተለየ ልጆቻቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ከድሃው ኢትዮጵያዊ በሚሰበሰብ ግብር በሶሊዳሪቲ አማካኝነት ውጪ ሃገር እየላኩ አስተምረዋል:: ደርግ ወደመቃብር ሲገባ እነዚህ በዲፕሎማትነት በየሃገሩ ተመድበው ሲሰሩ የነበሩ የአላማው አራማጆች ከነቤተሰቦቻቸው በያሉበትና አብዛኞቹም ወደ ካናዳ እና አሜሪካ ተሯሩጠው ገብተዋል::

ለከፍተኛ ትምህርት በመንግሥት (በኢሠፓ) በኩል ወደዉጪ ተልከው በዚያው የቀሩ በሃገር ውስጥ ከነበሩትም መሃል እንደምንም ያመለጡ ሁሉ ዛሬም ድረስ ኑሯቸውን በተረጋጋ ሁኔታ እየኖሩ ነው:: ዲሞክራቶች ከመሃላቸው የሉም ማለት ደግሞ አይቻልም:: ይሁንና የመንግሥቱ ኃይለማሪያም ስም ሲነሳ ሁሌም ኅሊናቸው ያንን ዘመን አብሮ እንደሚያነሳ ጥርጥር የለውም:: ዛሬ መንግሥቱ ኃይለማሪያም መጽሃፍ ጻፈ ሲባል ጀሌዎቹ ከያሉበት ብቅ ብቅ እያሉ ነጻ ዴሞክራሲ ነው ይጻፍ ብለው ቢጮሁ ምን ያስደንቃል? ለ እነርሱ የነጻነት መንገድ ይህቺ ናትና! በውነት አይደንቅም:: አንድ መጽሃፍ የሚሸጡ አታሚ ሰው ቢከስሩ ኢትዮጵያ ትጎዳለች ይሉናል! ሃገራቸው እየተቆራረጠች እነሱም ከቀያቸው በግድ እየተነሱ ለምትሸጥባቸው ኢትዮጵያውያኖችስ ማን አስታውሶ ይጻፍላቸው ይላሉ? ማን ይመስለዋል ብላችሁ ይሆን? ታሪክን ለመቅበር የምትከጅሉት?

ከዚህ ቀደም ታክሎ ተሾመ የሚባሉ ደራሲ የደም ዘመን በሚል መጽሀፋቸው ባሰፈሩት ተመሳሳይ የታሪክ ስህተት ጥያቄያዊ ማስተካከያ በመጻፌ በቀጥታ ለጽሁፌ የሚሆን

መልስ ከመስጠት ይልቅ ልክ ዛሬም እንደምናነበው ኢህአፓ ከአመታት በፊት የተረሳ ፓርቲ ነው፤ ከተሰዉት ጋር አክትሟል ሲሉ አትተው ገጹን ሞልተውታል:: ከአንድ ኢትዮጵያዊ አንደበት ይህንን መስማት ያሳዝናል:: ለመሆኑ ምን የሚሉት ዘመቻ ነው ይሄ?

ለፍትህና ለዴሞክራሲ ሲታገሉ መስዋዕት የሆኑ ወንድምና እህቶቻችን ታሪክ ለዘለዓለም ይኖራል! አቶ ታክሎ ተሾመ ምናልባት ከኢህአፓ ይልቅ ስለ ኢሠፓ ቢጽፉ የተሻለ እውቀትም ስላለዎ ይሳካልዎት ይሆናል የሚል እምነት አለኝ።

የመነጋገሪያ ጉዳዩ በተሰዉ ወንድሞችና እህቶቻችን ታሪክ ዙሪያ አልያም ደግሞ በመጽሃፍ ዙሪያ ሆኖ ሳለ የኢህአፓ እድሜና አመራሮች ጉዳይ ላይ ማንቀላፋት ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው?

የመንግሥቱን መጽሃፍ መታተም መቃወም ስለምን ያስደንቃል? ከሩብ ሚሊዮን የሚልቁ ኢትዮጵያውያንን ጨፍጭፏል:: ሴቶችን በአካላቸው ጸያፍ ድርጊት ፈጽሟል:: ወላጆችን የልጆቻቸውን አካል ቆርጠው አጉርሰዋል:: ደማቸውን በጨርቃቸው አሳፍሰዋል:: የወጣቶችን ሬሳ ከምሮ በእሳት አቃጥሏል:: ይህ ሠው ለፍርድ መቅረብ ይገባዋል!!!! ስህተት ያለበት ጥያቄ ነው እንዴ ይሄ??? መልሱን ከቀይ ሽብር ጠበቆች እጠብቃለሁ::

በአረመኔው መንግሥት የግፍ መፈጸሚያ ቤት በነበርኩበት ጊዜያት ውስጥ በኛ ላይ ይደርስ የነበረውን ሰቆቃ ሳስታውስ ከማይረሱኝ ውስጥ መክብብ ዘመድኩን የመጀመሪያው ነው:: መክብብ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴክኒዮሎጂ ፋኩልቲ አራተኛ ዓመት ተማሪ ነበር። የእድገት በህብረ ዘመቻ በሲዳሞ ውስጥ ዋደራ በምትባል ወረዳ ዘምቷል:: መክብብ በአረመኔዎቹ የደርግ መርማሪዎች በሚደርስበት ከፍተኛ ስቃይ እግሩን በፈላ ዘይት ውስጥ ነክረውት ጣቶቹ ረግፈዋል:: የቀኝ እጁን አጥንት ሠብረውት በፍጹም እጁን ማዘዝ የማይችል ሰው ሆነ:: በእግሩ ጣቶች መውለቅ ምክንያት መራመድም ሆነ ራሱን ችሎ መንቀሳቀስ አይችልም:: እንደዚያ ሆኖ በመጨረሻው ቀን ጥዋት ሊረሽኑት ከክፍሉ ውስጥ እየጎተቱ መኪናቸው ላይ ሊጭኑ ሲያወጡት "**የጭቁኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ያቸንፋል! ድል የኢትዮጵያ ህዝብ ነው!**" እያለ መዝሙር እየዘመረ ነበር የሄደው::

መክብብ ዘመድኩን በተወሰኑ የታሪክ መጻህፍት ውስጥ ተጠቅሷል::
የሞተለት ዓላማ ነው እሱን የሚያስታውሰው::
የታገለለት ህዝብና ሃገር ነው ታሪኩን የሚቀርጸው::
በጽናት የቆመለት ፓርቲ ነው የሚዘክርለት::
ይህንን እና ሌላውን ቀሪ (ሙሉ) ታሪክ ወደፊት እኔ ራሴ እጽፈዋለሁ::

ከዚህም ይበልጥ የሚያሳዝነው ቤተሰቦቹ ምግብ ይዘውለት ሲመጡ ወታደሮቹ ልብሱን አውጥተው ሰጧቸው። በዚያን ጊዜው ቋንቋ ልብስ መመለስ ልጃችሁ ተገድሏል ማለት ነው:: ይሄኔ ቤተሰቦቹ ሃዘናቸውን መቋቋም አልቻሉም ነበር። አረመኔዎቹ ይህ አልበቃ ብሏቸው ቤታቸው ድረስ በመሄድ ሃዘንተኛውን በትነው፤ ቤተሰቦቹን ልጃቸው የተገደለበትን የጥይት ዋጋ እንዲከፍሉ ጠይቀዋቸዋል::
እናታቸው ዛሬም በህይወት ይገኛሉ:: ሌሎችም ይህንን ሁኔታ የሚያውቁና እንደኔ መመስከር የሚችሉ በህይወት አሉ::

የሰው ልጅ ከኅሊናው ሊሸሽ ከቶም አይቻለውም:: ቀጥተኛና እውነተኛ ፍርድ መስጠት ነጻነትን ያስገኛል!

በኮሎኔሉ መጽሃፍ ዙሪያ ከተወለዱ ጽሁፎች የተረዳሁት በትግሉ የተሰዉትን ኢትዮጵያውያን ዓላማና ግብ ላይ ያለማተኮርን ነው። ይህ ደሞ ከምንም በላይ ከሚያሳምሙኝ ነገሮች ዋናው ነውና እኔም እንደነሱ ያለችሎታዬ ለመጻፍ እገደዳለሁ::

አረመኔዎች እና ህዝብን ያጠፉ ወንጀለኞች መቼም ይሁን መቼ በደም የተነከረ እጃቸውን ተይዘው ለፍርድ ይቀርባሉ !

የሰማዕታት ደም ይፋረዳቸዋል!
ፍትህ ያለመጓደል እንዲጸና እንታገላለን !

እናቸንፋለን !

ታህሳስ 2004

mesfinadola@googlemail.com